# የዐቢይ አሥተዳደር ዜጎች የዜግነት መብታቸው ይጠበቅላቸው ዘንድ

# አሮሞ መሆን ግዴታ ነው ብሏል!!

የዐቢይ አሥተዳደር በአዲስ አበባ ዳርቻ በተለያዩ ስፍራዎች ያሉ ወገኖቻችንን ቤቶቻቸውን እላያቸው ላይ እየናደ እያፈረሰ በሽዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ቤት አልባ በማድረግ አማራጭ መጠለያ ሳያቀርብ ወይም ሳያዘጋጅ ጎዳና ላይ በመጣል ከፍተኛ ግፍ ፈጽሟል፡፡

ለውጥ መጣ ሲባል ብዙ ዜጎች ተስፋ ካደረጉት ነገር ዋነኛው "የዜጎች መሠረታዊ መብት ይከበራል!" የሚለው ነበር፡፡ መጠለያ የማግኘት መብት ከዜጎች መሠረታዊ መብቶች አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ የአንድ ሀገር መንግሥት በቻለው አቅም ሁሉ የዜጎችን መሠረታዊ መብቶች የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡ በእኛ ሀገር ግን በዘመነ ወያኔ ሲፈጸም የቆየውና እየተፈጸመም ያለው ዜጎች በራሳቸው ጥረትና ግረት ከገበሬዎች መሬት እየገዙ መሠረታዊ መብቶቻቸውን ለማሟላት የቀለሱትን ደሳሳ ጎጆ በማፍረስ መሠረታዊ መብትን የማሳጣት ግፍ ነው ሲፈጸም የኖረውና እየተፈጸመም ያለው፡፡

ባለፈው ጊዜ በተለምዶ ቆሸ ተብሎ በሚጠራው የአዲስ አበባ አካባቢ በወገኖቻችን ላይ አደጋ በደረሰ ጊዜ "በቆሸ አደጋ የወያኔ መንስኤነት እና የችግሩ ዘለቄታዊ መፍትሔ!" በሚል ርእስ በጻፍኩት ጽሑፌ ላይ ይሄንን ብየ ነበር፦

http://www.ethiopanorama.com/?p=46831

"""......ለመሆኑ እነኝህ ወገኖቻችን በቦታው ለመኖር ፈጽሞ በማይመቸውና ለጤና አደገኛ በሆነ ቆሻሻ ሥፍራ ላይ ሔደው ለመስፈር ምን አስገደዳቸው??? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል፦

ዜጎች በሀገራቸው ጤንነታቸውና ደኅንነታቸው ተጠብቆ ሠርቶ የመኖር፣ መጠለያ የማግኘትና የመሳሰሉት መሠረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶላቸው የመኖር የማይጣስ የማይገሰስ ሙሉ መብት አላቸው፡፡ የየትኛውም ሀገር ሕገመንግሥት ይሄንን መብት ለዜጎቻቸው ያረጋግጣል፡፡ ይህ መብት በየትኛውም ሁኔታ ሊጣስ ሊገሰስ ሊገፈፍ የማይችል ሰብአዊ መብት ጭምርም ነው፡፡ መንግሥት ነኝ የሚል አካል ይሄንን የማሟላት ግዴት አለበት፡፡ ልብ በሉ መልካም ፈቃድ ሳይሆን ግዴታ ነው ያለበት፡፡ የአንድ ሀገር መንግሥት በምንም መልኩ ይሄንን መሠረታዊ የዜጎች መብት ሊገፍ፣ ሊነፍግ አይችልም፡፡

የአንድ ሀገር መንግሥት ግዴታና ኃላፊነቱ የሀገሪቱንና የሕዝቧን ህልውናና ደኅንነት ከመጠበቅ ባሻገር ከገጠር እስከከተማ ያለውን መሬት ለዜጎች አብቃቅቶ የማከፋፈሉን ፍትሐዊ ሥራ መሥራትና ዜጎች ከሀገራቸው ሊያገኙት የሚገባቸውን መሠረታዊ ጥቅም እንዲያገኙ ማስቻል ነው ግዴታውና ኃላፊነቱ፡፡ ምክንያቱም በሕዝብ ጥቅሞችና ጉዳዮች ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ የመወሰን ሥልጣንና ኃላፊነት ያለው ሕዝብ እንጅ መንግሥት ስላልሆነ፡፡ መንግሥት የሕዝብን ውክልና ይዞ የሕዝብን ጥያቄዎችና ፍላጎቶች ማስፈጸም ብቻ ስለሆነ ተግባሩ፡፡

ለሀገር ኢኮኖሚ (ምጣኔ ሀብት) እድገት ከመሬት ሽያጭ ከሚገኝ መጠነኛ ገቢ ይልቅ ዜጎች የመሬት ባለቤት ሆነው መሬቱ ላይ የሚፈጥሩት ሀብት ነው ሀገርን ሊለውጥ ሊያበለጽግ የሚችለው፡፡ ያደጉ ሀገራት ተሞክሮ የሚያሳየን ይሄንን ነው፡፡ ቁልፉ አስተሳሰብ ይሄ ከሆነ ሊሠራ የሚገባው ሥራ ዜጎችን በሰፊው የመሬት ባለቤት ማድረጉ ነው እንጅ የመሬት ባለቤትነትን መብት ማሳጣት አይደለም፡፡ ይህ ከተደረገ ግን ውሳኔው ሥልጣን የያዘን አካል ጥቅም የሚያስከብር ቡድናዊ ውሳኔ እንጅ የሀገርን ጥቅም የሚያስጠብቅ ሕዝባዊ ውሳኔ አይሆንም፡፡

ምን ያህሎቻችን ከላይ የጠቀስኩትን መሠረታዊ የሕዝብ ወይም የዜጎችን መብት እንደምናውቅና ይህን መብታችንንም ማስከበር፣ ማስጠበቅ እንዳለብን እንደምንገነዘብ አላውቅም፡፡ እንደማየው ሕዝቡ ይሄንን መሠረታዊ የዜጎችን መብት የሚያውቅ አይመስለኝም፡፡ መንግሥት ነኝ ከሚለው አካል ችሮታን ሲጠብቅ እንጅ የመንግሥት ግዴታው እንደሆነ አውቆ መብቱ እንዲጠበቅለት ሲጠይቅ ብሎም ሲያስገድድ አላይምና፡፡

መንግሥት ለባለሀብቶች በሽያጭ የቤት መሥሪያ መሬትና መሠረተ ልማት ማቅረብ ብቻ ሳይሆን አቅሙ በፈቀደለት መጠን ከ 90 ከመቶ በላይ የሚሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ቁጥር ለምንይዘው ቤት የመሥራት አቅም ለሌለን ድሀ እና የድሀ ድሀ ዜጎችን መሠረታዊ መብት የማሟላት ግዴታም ጭምር አለበት፡፡ ይሄኔ ነው ሀገር የሕዝብ መሆኗ እርግጥ የሚሆነው፡፡ ይሄንን እናውቃለን ወይ???

ወያኔ መንግሥት ነኝ እንደማለቱ ይሄንን ግዴታውን የመወጣት ግዴታ ነበረበት፡፡ ወያኔ ግን እንኳንና የዜጎችን መብትና የእሱንም ግዴታ በማክበር ቤት የመገንባት አቅም ላላቸው ዜጎች መሬት በመስጠት፣ ቤት የመገንባት አቅም ለሌላቸው ዜጎች ደግሞ የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን አቅሙን ያገናዘበ የኪራይ ዋጋ የሚጠይቁ የኪራይ ቤቶችን ገንብቶ በማቅረብ ዜጎች መጠለያ እንዲኖራቸው በማድረግ የዜጎችን መሠረታዊ መብትና ጥቅም ሊጠብቅ፣ ሊያከብር፣ ግዴታውንና ኃላፊነቱንም ሊወጣ ይቅርና ይህ በመንግሥት ስም ራሱን ያስቀመጠው የወንበዴ ቡድን ከከተማ እስከገጠር አስቀድሞ የመሬት ይዞታ የነበራቸውን ወገኖች ሳይቀር መሬታቸውን እየነጠቀ ለባዕዳንና ለባለሀብቶች በመቸብቸብ ዜጎች በዜግነታቸው ከሀገራቸው ሊያገኙት የሚገባቸውን ጥቅምና መሠረታዊ መብት አሳጥቷል፣ ነጥቋል፣ ገፏል፣ ሀገሪቱንም የባለሃብቶች ብቻ አድርጓታል፡፡ በዚህ ዝርፊያውም እራሱን በከፍተኛ ደረጃ በማድለብ ላይ ይገኛል፣ መሬትን የፖለቲካ (የእምነተ አሥተዳደር) ዋነኛ መጠቀሚያ መሣሪያው አድርጎ በመጠቀምም የግፍ አገዛዙን ዕድሜ ለማራዘም ጥረት እያደረገበት ይገኛል፡፡

እነኝህ ወገኖቻችን ለኑሮ የማይስማማ፣ ለጤና አደገኛ በሆነው ቆሻሻ ስፍራ ላይ ሔደው ለመሥፈር የተገደዱት ማንም ሊገስሰው፣ ሊሸረው የማይችል በዜግነታቸው በሀገራቸው መጠለያ አግኝተው ጤናቸውና ደኅንነታቸው ተጠብቆ የመኖር መብት እንዳላቸው ተረድተው በራሳቸው ወጪ አንድ ጥግ ላይ ጎጆ ቢጤ ቀልሰው ለመኖር ሲሞክሩ "የጨረቃ ቤት ነው፣ ሕገወጥ ሰፋሪዎች ናቹህ!" እያለ በሌለ አቅማቸው የቀለሷቸውን ጎጆዎች እያፈራረሰ መድረሻ ቢያሳጣቸው ነው "ይህ ስፍራ ቆሻሻ ነውና አይፈለግም ይሆናል!" ብለው እዚያ ቆሻሻ ላይ ደሳሳ ጆጎ እየቀለሱ፣ የላስቲክ (የተለጥ) ቤት እየወጠሩ ለመስፈር የተገደዱት፡፡

የደርግ መንግሥት ይሄንን የዜጎችን መሠረታዊ መብትና የመንግሥትነትን ግዴታ በመገንዘብ ይመስላል የመሬት ላራሹንና ትርፍ የከተማ ቤትን የመውረስ አዋጆችን በማወጅ መሬት ላልነበረው ዜጋ የመሬት ባለቤት አድርጓል፣ ቤት የመሥራት አቅም ላላቸው የከተማ ነዋሪዎች ለካርታ (ንድፈ ምድር) እና ለተመሳሳይ ጉዳዮች ማስፈጸሚያ በጣም አነስተኛ ወጪ በማስከፈል በነጻ ቤት የመገንቢያ መሬት ለዜጎች ሲያቀርብ ነበር፡፡ ቤት የመገንባት አቅም ለሌላቸው ወገኖች ደግሞ እንደየአቅሙ ከሃምሳ ሳንቲም ጀምሮ በጣም አነስተኛ ኪራይ የሚከፈልባቸውን የኪራይ ቤቶችን ገንብቶ እንዲሁም በአዋጅ የተወረሱ ቤቶችን በማቅረብ የዜጎችን መጠለያ የማግኘትን መሠረታዊ መብትና የመንግሥትነቱን ግዴታ ለማክበር፣ ለመጠበቅና ለመወጣት ጥረት ያደርግ ነበር፡፡

ወያኔ "መንግሥት ነኝ!" ካለ ይሄንን የደርግን ፈለግ መከተል ሲኖርበት ያልተከተለው "የሚከተለው ርዕዮተዓለም ከደርግ የተለየ ስለሆነ ነው!" እንዳንል የሚከተለው ርዕዮተዓለም ከደርግ የሚለይ አይደለም፡፡ ሁለቱም "እንከተለዋለን!" እያሉ የመጡት ሶሻሊዝምን ነው፡፡ ወያኔ የሚከተለው የኢኮኖሚ (የምጣኔ ሀብት) ሥርዓት ነጻ (ሊበራል) ቢሆን ኖሮ ከገጠር እስከ ከተማ መሬትን ከዜጎች እየነጠቀ ለባለሃብቶች ሊሸጥ ባልቻለ ነበር፡፡

ሙቱ የወያኔው መሪ አቶ መለስ ዜናዊ ይሄንና ተጓዳኝ ነገሮችን በተመለከተ በአንድ ወቅት ላይ ተጠይቀው ሲመልሱ ያለአንዳች ሐፍረትና የተጠያቂነት ስሜት ነበረ በብዙኃን መገናኛ "ከተማ ለቆ መውጣት ነው!" ብለው በመናገር አገዛዛቸው የአፓርታይድ (የመድሎ) ወይም ለባለሀብቶች ብቻ የቆመ አገዛዝ መሆኑን ያረጋገጡት!........

ዜጎች በዜግነታቸው መሠረታዊ መብታቸውና ጥቅማቸው ተከብሮላቸው በገዛ ሀገራቸው ተረጋግተው መኖር ካልቻሉ ዜጎች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ጥቅም፣ ሀገሬ ብሎ ለማለት የሚያስችላቸው መብት ሌላ ምን አለና? ነገ ጠዋት በዚህች ሀገር ላይ ጥቃት ቢቃጣ "ሀገሬ!" ብሎ ተነሥቶ ደሙን አፍስሶ አጥንቱን ከስክሶ ሉዓላዊነቷን የሚያስከብረው ማን ነው? መሬታችን ተነጥቆ የተሰጣቸው ባዕዳን ባለሀብቶች ናቸው እንዴ? ወይስ ጥቂት የናጠጡ ባለሀብት ዜጎቻችን? ይሄ ወያኔ መድረሻ ያሳጣው ድሀ ሕዝብ እና መሬቱ እየተነጠቀ ለባዕዳን እየተሰጠበት ያለው ገበሬ አይደለም ወይ? እንዲህ የደም ዋጋ ከፍሎ ያቆያትን እና ነገ አንድ ነገር ቢፈጠርም "ሆ!" ብሎ ተነሥቶ መራር መሥዋዕትነትን የሚከፍልላትን ዜጋ በምን ሒሳብ፣ በየትኛው መሥፈርት ነው ከገዛ ሀገሩ ሊያገኘው የሚገባው ጥቅምና መብት ተነፍጎት ባይተዋር፣ ተሳዳጅና የበይ ተመልካች ሊደረግ የሚገባው? እኮ በየትኛው ፍትሐዊ አሠራር? በወያኔ ዓይነቱ ኢፍትሐዊ የአፓርታይድ (የመድሎ) አገዛዝ ካልሆነ በስተቀር!!!

እናም የዋሁ ወገኔ ሆይ! የችግሩ መፍትሔ ብሔራዊ የሐዘን ቀን ማሳወጁ ሳይሆን ስንት ዋጋ ከፍለህ ያቆየሀትንና ወደፊትም የምትከፍልላትን ሀገርህን ነጥቆ የባዕዳንና የባለሃብቶች ብቻ ያደረገብህን፣ በገዛ ሀገርህ ተሳዳጅ፣ ተፈናቃይ፣ የበይ ተመልካች ያደረገህን አንባገነን የወንበዴ አገዛዝ ማስወገድ ነውና በየጊዜው በአገዛዙ የግፍ አስተዳደር መንስኤነት አንድ ነገር በተፈጠረ ቁጥር ማላዘኑን ትተህ የችግሮችህ ሁሉ ምንጭ የሆነውን ወያኔን ለመገርሰስ ቆርጠህ ተነሥ! ሳትውል ሳታድር ክንድህን በግፈኛው በጠንቀኛው አገዛዝ በወያኔ ላይ አንሣ! ይህን ማድረግ ካልቻልክ ግን ነገም ያንተ እጣ ከእነኚህ አደጋው ከደረሰባቸው ወገኖች የተለየ እንደማይሆን እወቀው!........ """ ብየ በመጻፍ ነበር የግፍ አገዛዙን ግፍ ለመግለጥ የሞከርኩት፡፡

ይሄው አሁን ደግሞ የዐቢይ አሥተዳደር ሰባት መቶ ሽህ ብርና ከዚያ በላይ ካሳ እየተከፈላቸው "መሬታቸውን ለልማት እንዲለቁ ተገረጉ!" የተባሉትን የአዲስ አበባ ዙሪያ ገበሬዎችን "በቂ ካሳ አልተከፈላቸውም፣ ሌሎች ጥቅሞችም አልተጠበቁላቸውም!" በማለት ጠቀም ያለ የማስተካከያ ክፍያና ጥቅማጥቅሞች ለመስጠት ደፋቀና እያለ ባለበት በአሁኑ ሰዓት ያለ የሌለ ገንዘባቸውን አውጥተው መሬት ከገበሬ ገዝተው ደሳሳ ጎጆ ቀልሰው እየኖሩ ያሉ በሽዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን "የጨረቃ ቤት ነው፣ ሕገወጥ ሰፋሪዎች ናቹህ፣ መሬት ወራሪዎች ናቹህ!" እያሉ ደሳሳ ቤቶቻቸውን እላያቸው ላይ አፍርሶ ሕፃናትን፣ አሮጊት ሽማግሎችን፣ አራስ እናቶችን ጎዳና ላይ ጥሎ አውሬ ጅብ እንዲበላቸው መስጠትን ምን ይሉታል???

ማንስ ነው መሬት ወራሪው??? ማንስ ነው ሕገወጥ ሰፋሪው??? መስፈርቱና መለኪያውስ ምንድን ነው??? እነኝህን የግፍ ሰለባ ዜጎችን "በቂ ካሳና ጥቅም አልተጠበቀላቸውም!" ብላቹህ ልታንበሸብሿቸው ከተዘጋጃቹህላቸው ገበሬዎች የሚለያቸው ምንድን ነው??? ለገበሬዎቹ እንድትቆረቆሩ ያደረጋቹህ የዜጎች መብት ጉዳይ ከሆነ እንዴት ለእነዚህ ወገኖች የዜግነት መብትም ሳትቆረቆሩ ቀራቹህ??? ለገበሬዎቹ በዚህ ደረጃ እላፊ ሔዳቹህ እንድታስቡ እንድትቆረቆሩ ያደረጋቹህ የዜጎች መብት ጉዳይ ከሆነ በተመሳሳይ ቤታቸውን ላፈረሳቹህባቸው ዜጎችም ቢያንስ እንኳ መጠለያ የማግኘት መሠረታዊና የዜግነት መብታቸው ነውና ሌላ የመጠለያ አማራጭ የማቅረብ ግዴታቹህን በማሰብ አማራጭ መጠለያ ማቅረብ አልነበረባቹህም ወይ??? ነው ወይስ በእናንተ ስሌት ዜጋ ማለት ኦሮሞ ብቻ ነው??? ዜጎች መሠረታዊ መብታቸው ይጠበቅላቸው ዘንድ ኦሮሞ መሆን አለባቸው ማለት ነው ወይ??? ይህ አሠራርስ የወያኔን የዘር መድሎ (Apartheid) አገዛዝ ማስቀጠል አይደለም ወይ???

ወገን ሆይ! ይሄ ግፍ በእነኝህ ወገኖች ብቻ ተፈጽሞ የሚቀር እንዳይመስልህ!!! እየተፈጸመ ያለው ግፍ ከኦሮሞ ውጭ ያለውን ዜጋ ሁሉ በቀጥታ ይመለከታልና ነገ እያንዳንዳችንን "ከፊንፊኔ ውጡልን!" ብለው የግፍ ጥቃታቸው ሰለባ ሳያደርጉን በፊት ነገ ሳንል ዛሬ ሁላችንም አጥብቀን ልናወግዘው ልንቃወመውና ልናስቆመው ይገባል!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com